**በግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር**

**በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት**

**ለገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ**

**አዲስ አበባ**

ጉዳዩ፡- **የኮሌጁን የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርትን ይመለከታል፤**

በርዕሱ የተጠቀሰውን የገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ የ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦችን የያዘ 33 ገጽ የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት (Final Management Letter) እና 22 ገጽ አባሪ በድምሩ 55 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን ልከናል። በመሆኑም በገጽ 56 በተመለከተው የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር ቅጽ መሰረት የተወሰዱ እርምጃዎች በአስቸኳይ እንዲላክልን እናሳስባለን።

ከሰላምታ ጋር !

ሰለሞን መብራቱ

የልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች

ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

ግልባጭ

- ☞ ለግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር ከ55 ገጽ አባሪ ጋር
- ☞ ለግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ከ55 ገጽ አባሪ ጋር

አዲስ አበባ

የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር

# በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት

# የገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ

## የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት

## የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት

ግንቦት 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## በግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር
## በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት
## የገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ
## የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት

### መግቢያ

ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ በአዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመሥሪያ ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት በቀድሞው እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር የ2009 በጀት ዓመት የሂሣብ መግለጫ ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ሂሳቡን ኦዲት አድርገናል፡፡

### ዓላማ

የዚህ ደብዳቤ ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶችን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ፣ የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቱና የኮሌጁ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱበት ለማድረግ ነው፡፡

### የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው የዓለም አቀፍ የመንግሥት ኦዲት ደረጃዎችን (INTOSAI/ISA) መሰረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል፡፡

### ኦዲታችን የሚያካትተው፡-

- ✓ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና መመርመርን፣
- ✓ የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣

- ✓ የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ለፌዴራል መንግሥት አጠቃላይ ዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ ዝግጅት አግባብነት ያላቸው መሆኑን፣ ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል።

ከዚህም በተጨማሪ የሂሳብ መግለጫዎቹ ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና መመርመርን ይጨምራል።

የሂሳብ መግለጫዎቹ ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል። አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል።

በመሆኑም በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት የአሰራርም ሆነ የሂሳብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሳብ መግለጫውን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም።

የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ከዚህ ጋር የተያያዙ ግድፈቶችና ስህተቶች ሁሉ ሊታወቁ የሚችሉት ይህን አስመልክቶ ሰፊ ጊዜ በመውሰድ ልዩ የዝርዝር ኦዲት በጥልቀት ሲከናወን መሆኑን እንገልጻለን።

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኃላፊነት ነው።

## የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

የገዋኔ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅን በ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች ረቂቅ ሪፖርት ላይ ምላሽ እንዲሰጥ የካቲት 13 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር OFAGF-02.7/2/4 በተጻፈለት ደብዳቤ መሰረት ኮሌጁ መጋቢት 7 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር 02/ረ/-06/148-63 በጻፈው ደብዳቤ ምላሽ ሰጥቷል። በመሆኑም ለሥራ አመራሩ የተዘጋጀው የመጨረሻው ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 1. የተሰብሳቢ ሂሳብ

#### 1.1 በወቅቱ ያልተወራረደ የተሰብሳቢ ሂሳብ፤

##### 1.1.1 ግኝት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ፣ በመመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል። በመሆኑም ኮሌጁ በዚሁ መሰረት የሚፈጽም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በሂሳብ መደብ 4203 ብር 75,636.52 ከአንድ ወር አስከ አንድ ዓመት ድረስ ሳይወራረድ (ሳይሰበሰብ) የቆየ ሲሆን፣ ብር 226,541.91 ደግሞ ከአንድ ዓመት በላይ አስከ አምስት ዓመት ድረስ ሳይወራረድ (ሳይሰበሰብ) የቆየ መሆኑ፤
- በሂሳብ መደብ 4211 ብር 107,423.21 ከአንድ ወር አስከ አንድ ዓመት ድረስ ሳይወራረድ (ሳይሰበሰብ) የቆየ ሲሆን፣ ብር 462,408.06 ደግሞ ከአንድ ዓመት በላይ አስከ አምስት ዓመት ድረስ ሳይወራረድ (ሳይሰበሰብ) የቆየ መሆኑ፤

በድምሩ ብር 872,009.70 ለረጅም ዓመት ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) መሆኑ ታውቋል። በ2007 ሂሳብ ኦዲት ወቅት ሂሳቡ እንዲወራረድ

(እንዲሰበሰብ) አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም ሂሳቡ ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 1 ተያይዟል)

### 1.1.2 *ሥጋት*

- ☞ በተሰብሳቢ ሂሳቦች ላይ ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል ካልተደረገ የመንግሥት ገንዘብ ሳይሰበሰብ ሊባክን ይችላል።
- ☞ ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ማረጋገጥ አይቻልም።
- ☞ ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ ከነማን እንደሚሰበሰቡ ለማወቅ አያስችልም።

### 1.1.3 *የማሻሻያ ሃሳብ*

በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች እንዲሰበሰቡ፣ ሊሰበሰቡ የማይችሉ ከሆነ ግን በመመሪያው መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ፣ እንዲሁም የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች በወቅቱ እንዲወራረዱ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል። በተጨማሪም ተቀጽላ ሌጀር ላልተዘጋጀላቸው ሂሳቦች ደግሞ ተቀጽላ ሌጀር እንዲዘጋጅላቸው መደረግ ይኖርበታል።

### 1.1.4 *የሥራ አመራሩ ምላሽ*

በወቅቱ ያልተወራረደውን ሂሣብ አስመልክቶ የተሰጠውን አስተያየት መነሻ በማድረግ በሂሳብ መደብ ቁጥር (በኮድ ቁጥር) 4203 እና በ4211 በወጪ ተመዝግቦ የነበረውን የብር 872,009.70 የተሰብሳቢ ሠነድ ክምችት በብር 213,949.76 ዝቅ እንዲል (እንዲቀንስ) የተደረገ ሲሆን በቀሪው ተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የማወራረድ ሂደቱ የሚቀጥል ይሆናል።

### 1.1.5 *የኦዲተሩ አስተያየት*

ተሰብሳቢ ሂሳቡን ለማወራረድ የሚደረገው ጥረት እንዲቀጥል እያሳሰብን ተወራርዷል የተባለው ሂሳብ አግባብነትና ትክክለኛነት በቀጣይ ኦዲት ወቅት የሚረጋገጥ ይሆናል።

## 2. <u>የተከፋይ ሂሳብ</u>

### 2.1 <u>በወቅቱ ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ</u>፤

#### 2.1.1 <u>ግኝት</u>

በኮሌጁ የሚገኙት ተከፋይ ሂሳቦችን ተገቢነት ለማረጋገጥ እንዲሁም መሥሪያ ቤቱ ያለበትን ተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል የሚከፍል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በተለያዩ የተከፋይ ሂሳብ ኮዶች (መደቦች)፡-

- ☞ ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ ብር 3,948.35፣
- ☞ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ ብር 170,171.42፣

በድምሩ ብር 174,119.77 በፋይናንስ ደንብና መመሪያው መሰረት በወቅቱ ያልተከፈለ መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 2 ተያይዟል)

#### 2.1.2 <u>ሥጋት</u>

የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ካልተወሰደ የሂሳብ ሪፖርቱን ተዓማኒነት ሊያሳጣው ይችላል።

#### 2.1.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ኮሌጁ ያለበትን ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል በወቅቱ እንዲከፍል፤ ይህ የማይሆን ከሆነ የተከፋይ ሂሳቦቹ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ መደረግ ይኖርበታል።

#### 2.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

ኮሌጁ ከተለያዩ ድርጅቶችና ግለሰቦች የተከፋይ ሒሳብ በ2010 ዓ.ም እያንዳንዱን በጥልቀት በመለየትና በማደራጀት ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እንዲሁም ለሚመለከታቸው አካላት ክፍያውን በደንብና በመመሪያው መሰረት በማዘጋጀት ይፈጸማል።

## 2.2 በወቅቱ ያልተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤

### 2.2.1 ግኝት

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የካቲት 2002 በገኸሮው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም ባወጣው መመሪያ ቁጥር 27/2002 ክፍል 6 ተራ ቁጥር 4 ወኪሉ በወሩ ውስጥ ካከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ቀንሶ የያዘውን ታክስ ከወሩ የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለታክስ ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ገቢ የማድረግ ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል። ሆኖም ኮሌጁ በበጀት ዓመቱ ከነሀሴ 2008 ዓ.ም እስከ ሚያዚያ 2009 ዓ.ም ድረስ ታክስ ከሚከፈልበት ግብይት ላይ ቀንሶ የያዘውን ብር 702,666.20 በመመሪያው ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ለግብር ሰብሳቢው በለሥልጣን ገቢ ማድረግ ሲገባው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30 ቀን 2009 ገቢ ያደረገ መሆኑ ታውቋል። ከዚህም በተጨማሪ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች በተሟላ መልኩ ከወጪ ማስረጃዎቹ ጋር ሳይያዙ በጥራዙ ላይ የሚገኙ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል። (ለዝርዝሩ አባሪ 3 ተያይዟል)

### 2.2.2 ሥጋት

የተጨማሪ እሴት ታክሱ በህጉ መሰረት ለሚመለከተው አካል በወቅቱ የማይከፈል ከሆነ፡-

- ☞ ኮሌጁ ለቅጣት ሊዳርግ ይችላል።
- ☞ መንግሥት በወቅቱ ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ ሊያጣ ይችላል።
- ☞ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል።
- ☞ በውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል።

### 2.2.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ኮሌጁ ቀንሶ ያስቀረውን የተጨማሪ እሴት ታክስ በመመሪያው መሰረት ወቅቱን ጠብቆ ለግብር ሰብሳቢው ባለስልጣን ገቢ ማድረግ ይኖርበታል። የደረሰኞቹም ኮፒ ከወጪ ሂሳቡ ጋር ሊያያዙ ይገባል።

### 2.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

ለመንግሥት ወቅቱን ጠብቀው ገቢ ያልሆኑ የታክስ ተከፋይ ሂሳቦችን በሚመለከት ለቀረበው ጥያቄ የችግሩ መንስኤ፤ በስራ ክፍሉ ይህንን የሚያሰባስብ፣ የሚያደራጅና የሚፈፅም የሰው ኃይል ተሟልቶ አለመገኘት ሳቢያ የተፈጠረ እክል መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ሆኖም ግን የስራ ክፍሉን በሚፈለገው የሰው ኃይል ለማደራጀት በመጣር ላይ የምንገኝና በበላይ ኃላፊዎችም ዘንድ ችግሩ የሚታወቅ መሆኑን እየገለፅን በቀጣይ ባለን አቅም ለደንቡ ተፈፃሚነት ቅድሚያ በመስጠት አስፈላጊውን ማስተካከያ እናደርጋለን፡፡

## 2.3 በወቅቱ ያልተከፈለ የቅድሚያ ክፍያ ግብር፤

### 2.3.1 ግኝት

በገቢ ግብር አዋጅ 286/2002 አንቀጽ 53/3 መሠረት ከተከፋይ ሂሳብ ግብሩን ቀንሶ ገቢ ማድረግ ያለበት መሥሪያ ቤት በወሩ ውስጥ ከተከፈሉ ሂሳቦች ላይ ቀንሶ ቀሪ ማድረግ የሚገባውን አጠቃላይ ሂሳብ ከወሩ የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ቀናት ውስጥ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ሆኖም ኮሌጁ ከነሀሴ 2008 ዓ.ም እስከ ግንቦት 2009 ዓ.ም ድረስ ታክስ ከሚከፈልበት ግብይት ላይ ቀንሶ የያዘውን ብር 255,165.87 በመመሪያው ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ለግብር ሰብሳቢው በለሥልጣን ገቢ ማድረግ ሲገባው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ገቢ የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቅድሚያ ግብር የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች በተሟላ መልኩ ከወጪ ማስረጃዎቹ ጋር ሳይያዙ በጥራዙ ላይ የሚገኙ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ (ለዝርዝሩ 4 አባሪ ተያይዟል)

### 2.3.2 ሥጋት

የቅድሚያ ግብር ሂሳቡ በህጉ መሰረት ለሚመለከተው አካል በወቅቱ የማይከፈል ከሆነ፡-

☞ ኮሌጁ ለቅጣት ሊዳርግ ይችላል፡፡

☞ መንግሥት በወቅቱ ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ ሊያጣ ይችላል።
☞ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል።
☞ በውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል።

#### 2.3.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ኮሌጁ ቀንሶ ያስቀረውን የቅድሚያ ክፍያ ግብር በመመሪያው መሰረት ወቅቱን ጠብቆ ለግብር ሰብሳቢው ባለስልጣን ገቢ ማድረግ ይኖርበታል። ኮፒ ደረሰኞቹም ከወጪ ሂሳቡ ጋር ሊያያዙ ይገባል።

#### 2.3.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

ለመንግሥት ወቅቱን ጠብቀው ገቢ ያልሆኑ የግብር ተከፋይ ሂሳቦችን በሚመለከት ለቀረበው ጥያቄ የችግሩ መንስኤ፤ በስራ ክፍሉ ይህንን የሚያሰባስብ፣ የሚያደራጅና የሚፈፅም የሰው ኃይል ተሟልቶ አለመገኘት ሳቢያ የተፈጠረ እክል መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። ሆኖም ግን የስራ ክፍሉን በሚፈለገው የሰው ኃይል ለማደራጀት በመጣር ላይ የምንገኝና በበላይ ኃላፊዎችም ዘንድ ችግሩ የሚታወቅ መሆኑን እየገለፅን በቀጣይ ባለን አቅም ለደንቡ ተፈፃሚነት ቅድሚያ በመስጠት አስፈላጊውን ማስተካከያ እናደርጋለን።

## 3. የወጪ ሂሳብ

### 3.1 ከሥራ ለለቀቁ ሠራተኞች የተከፈለ ደመወዝ፤

#### 3.1.1 ግኝት

የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባወጣው የፌዴራል መንግሥት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4 ንዑስ አንቀፅ 10 ተራ ቁጥር 8 መሰረት ሠራተኞቹ በስራ ላይ ለመሆናቸው የቀረበ ማረጋገጫ መኖሩ ተረጋግጦ ደመወዝ መዘጋጀት እንዳለበት የተደነገገ ቢሆንም ኮሌጁ ይህን አሰራር ተግባራዊ ባለማድረጉ ኮሌጁን ለለቀቁ ለሁለት ሰራተኞች በጠቅላላው ብር 9,250.33 ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል። (ለዝርዝሩ አባሪ 5 ተያይዟል)

#### 3.1.2 ሥጋት

- ☞ በደመወዝ አከፋፈል ወቅት ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ካልተደረገ የመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ ሊወጣ ይችላል።
- ☞ በደመወዝ ላይ የሚደረገውን የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ክፍተት ሊያመለክት ይችላል።

#### 3.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ

አለአግባብ ለሠራተኞች የተከፈለው ደመወዝ ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል። ለወደፊቱም ሰራተኛ ሲለቅ የደመወዝ ክፍያ እንዳይፈጸም የሰው ሀብት ዳይሬክቶሬት በወቅቱ ለፋይናንስ ክፍሉ የለቀቁ ሰራተኞችን ዝርዝር ማሳወቅ ይኖርበታል። ሂሳብ ክፍሉም አለአግባብ ክፍያ እንዳይፈጸም ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል።

#### 3.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

ኮሌጁን ሲያገለግሉ ቆይተው በዝውውር ለቀው ለሄዱ ሁለት ሠራተኞች አለአግባብ የተከፈለው ያልሰሩበት ደመወዝ ተመላሽ እንዲሆን ታዟል። በዚሁ መሠረት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሠራተኞች ከኮሌጁ ከተሰናበቱ በኋላ አለአግባብ የተከፈላቸውን የመንግሥት ገንዘብ ተመላሽ እንዲሆን በአሁኑ ወቅት ሠራተኞቹ ለሚሰሩበት መስሪያ ቤት ደብዳቤ ተጽፎ ምላሹ በመጠበቅ ላይ ይገኛል።

### 3.2 በጀት ስለመፈቀዱ በሚመለከተው አካል ያልተፈረመ ስለመሆኑ፤

#### 3.2.1 ግኝት

የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሀሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 3/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 6 ማናቸውም የሳጥንና የባንክ ሂሳብ ወጪ ከመሆኑ በፊት በጀት ስለመኖሩ በቅድሚያ መረጋገጥ እንዳለበት ተመልክቷል። በመሆኑም በኮሌጁ የተፈጸሙት ክፍያዎች በመመሪያው መሰረት ተግባራዊ መሆናቸውን ለማረጋገጥ

በናሙና ኦዲት ሲደረግ ብር 1,870,124.83 በወጪ ማስመስከሪያ ደረሰኞች ላይ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በጀት ስለመኖሩ በፊርማ ያልተረጋገጠ መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 6 ተያይዟል)

### 3.2.2 ***ሥጋት***

- ☞ ለየሂሳብ መደቦቹ (ኮዶች) የተፈቀደ በጀት ሳይኖር ክፍያ ሊፈጸም ይችላል።
- ☞ በበጀት ቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ያለውን ክፍተት ሊያመለክት ይችላል።

### 3.2.3 ***የማሻሻያ ሃሳብ***

ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ለወጪው በጀት የተያዘ ለመሆኑ በቅድሚያ በወጪ ማስመስከሪያ ደረሰኝ ላይ እንዲረጋገጥ መደረግ ይኖርበታል።

### 3.2.4 ***የሥራ አመራሩ ምላሽ***

በወጪ ርዕስ በጀት መኖሩ በሚመለከተዉ ሰራተኛ ሳይረጋገጥ የተፈፀሙ ክፍያዎችን በሚመለከት ለቀረበዉ ጥያቄ በወቅቱ ይህንኑ የሚያረጋግጠዉ ሰራተኛ የቤተሰብ ችግር ገጥሞት በተሰጠዉ የፈቃድ ጊዜ ሳይመለስ በመቅረቱ ይህንን የስራ መደብ የሚሸፍን ሠራተኛ በዝዉዉር እስክንመድብ ድረስ በተፈጠረዉ ክፍተት የተፈፀመ ስህተት ነዉ። ይሁንና በተመሳሳይ ለሚገጥሙ ሁኔታዎች የአደጋ ተጋላጭነት ስጋት እንዳለዉ እየተገነዘብን የስራ ቦታዎችን ለቀዉ በሚሄዱ ሰራተኞች ምትክ ክፍተቱን የሚሸፍን ሠራተኛ በአፋጣኝ መመደብ እንዳለብን አዉቀናል። ይሁንና ያልተፈረሙ ሰነዶች ተጠያቂነት ያላቸዉ በመሆኑ እንዲሟሉ ይደረጋል።

## 3.3 ***በፋይናንስ መመሪያው መሰረት ያልተመዘገበና ያልተፈጸመ የኮንትራክተር ክፍያ፤***

### 3.3.1 ***ግኝት***

በኮሌጁ ለህንፃ ተቋራጭ የሚፈጸም ክፍያ በውሉ መሰረት የተፈጸመ እና የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያን ተከትሎ የሚመዘገብ መሆኑን ለማረጋገጥ

ኦዲት ሲደረግ ኮሌጁ በገዋኔ ወረዳ በሙክቲዲላ (አሻካ) ቀበሌ ውስጥ በሚገኘው የገዋኔ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ውስጥ፡-

1. የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ፣
2. የቆሻሻ ማስወገጃ ግንባታ፣
3. የህንጻ ጥገና፣
4. የውሃ መስመር ዝርጋታ፣
5. የበግና የፍየል እርባታ ሰርቶ ማሳያ ግንባታ፣
6. የእንስሳት ጤና ክልኒክ ግንባታ፣ እንዲሁም
7. የዶሮ እርባታ ግንባታ እያከናወነ መሆኑ ይታወቃል።

ኮሌጁ ከተለያዩ የህንጻ ተቋራጮቹ ጋር ባደረገው ሥምምነት መሰረት የተፈጸሙ ክፍያዎችና የአመዘጋገብ ሥርዓቱ መመሪያውን ተከትሎ የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ብር 2,317,345.94 በወጪ ያልተመዘገበ ሂሳብ መኖሩ፤
- ብር 1,444,970.18 በብልጫ የተመዘገበ የወጪ ሂሳብ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለአሼቶ ኢንጂነሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የተፈጸመው ክፍያ ብር 71,530.00 በአማካሪው ከቀረበው የክፍያ ሰርተፊኬት በላይ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤
- ብር 2,835,538.85 ተመላሽ ተደርጎ ያልተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ መኖሩ፤
- ብር 31,263.20 ተመላሽ ያልተደረገ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ መኖሩ፤
- ብር 310,000.00 ከውል ውጭ በብድር ተሰጥቶ ተመላሽ ያልተደረገ ሂሳብ መኖሩ፤
- ብር 224,457.86 በብልጫ የተቀነሰ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሂሳብ መኖሩ፤
- ብር 457,125.54 ያልተቀነሰ የተጨማሪ እሴት መኖሩ፤
- ብር 16,408.30 ያልተቀነሰ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ መኖሩ፤
- ብር 237,770.00 ተመላሽ ተደርጎ ያልተመዘገበ የመያዣ ሂሳብ መኖሩ፤
- ብር 361,794.57 ያልተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ መኖሩ፤

- ብር 22,055.84 በብልጫ የተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ መኖሩ፤
- ከላይ በተመለከቱት ልዩነቶች ምክንያት ብር 3,131,010.88 በብልጫ የተከፈለ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ መኖሩ፤
- ከአሊ ሞሚን ጠቅላላ የውሃ ነክ ስራዎች ተቋራጭ ጋር ለውሀ መስመር ዝርጋታው ፕሮጀክት የተጨማሪ ሥራዎች ውል ሳይኖር ብር የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ ብር 408,459.30 ተጨማሪ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤

ታውቋል። በ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅት ለልዩነቱ ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም ሳይሰተካከል ባለበት ሁኔታ እንደሚገኝ ለመገንዘብ ተችሏል። (ለዝርዝሩ አባሪ 7 ተያይዟል)

### 3.3.2 ሥጋት

በአመዘጋገቡ ላይ በሚታየው ስሕተት ምክንያት፡-

- የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያመለክት ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ።
- ሊቀነስ የሚገባው ገንዘብ ሳይቀነስ ሊቀር ይችላል።
- ሊከፈል የሚገባው ሒሳብ ላይከፈል ይችላል።
- ለመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ይችላል።

### 3.3.3 የማሻሻያ ሃሳብ

በአመዘጋገብ ላይ ለታዩ ክፍተቶች ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራ ይደረግ ዘንድ ተገቢ የሆነ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል።

### 3.3.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

የችግሩ መንስኤ ክፍያው በሚፈጸምበት ወቅት በፋይናንስ ክፍል በነበረው አነስተኛ የሰው ኃይል እና ለሥራው የሚያስፈልገው በቂ ልምድና የክህሎት ክፍተት ሳቢያ የተከሰተ መሆኑን በመግለጽ የአመዘጋገብ ስህተቱን የምናርም መሆኑን ቀደም ሲል ማሳወቃችን ይታወሣል። ይሁንና ለተፈጠረው ስህተት አሁንም አስፈላጊውን ማስተካከያ ለማድረግ የአቅም ውስንነት ያለብን መሆኑን ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤታችን በማሳወቅ ይህንኑ

ችግራችን ለያግዘን የሚችል ሙያተኛ በሚቻለው መንገድ ተፈልጎ እንዲላክልን ጠይቀን ሙያተኞቹን በመጠባበቅ ላይ የምንገኝ ሲሆን በቅርብ ጊዜ ውስጥ በሚገኘው የቴክኒክ ድጋፍ የተፈጠረውን ስህተት በማረም የደረሰንበትን ደረጃ የምናሳውቅ ይሆናል፡፡

## 3.4 <u>በግንባታ ሥራዎች ላይ የታዩ ክፍተቶች</u>፤

### 3.4.1 <u>ግኝት</u>

ኮሌጁ ከተለያዩ የግንባታ ተቋራጮች ጋር ውል ገብቶ የተለያዩ የግንባታ ስራዎችን እያከናወነ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህም መሰረት የተጠናቀቁት የግንባታ ስራዎች ለታለመላቸው አላማ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. ኮሌጁ ከአሊ ሞሚን ጠቅላላ የውሀ ነክ ስራዎች ተቋራጭ ጋር ለውሀ መስመር ዝርጋታ ግንባታ በብር 7,379,375.32 ውል የፈጸመና ሥራውም ተጠናቆ ከተቋራጩ ጋር ጊዜያዊ ርክክብ የፈጸመ ቢሆንም፡-
   - 1.1. በውሀ መስመሩ ላይ ተዘርግተው የነበሩት በርካታ የውሀ ማስተላለፊያ ቧንቧዎች ከመሀል የተነሱና በገዋኔ ከተማ በሚገኘው ውሀ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ግቢ ውስጥ ሜዳ ላይ ተከማችተው የሚገኙ ሲሆን፣ በውሀ መስመሩ ላይ የቀሩት የውሀ ማስተላለፊያ ቧንቧዎችም ቢሆኑ አልፎ አልፎ የወላለቁ መሆኑ፤
   - 1.2. ኮሌጁ የውሀ መስመሩን ዝርጋት ርክክቡ ከፈጸመበት ከመስከረም 30 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ በወር ብር 60,000.00 የውሀ ማመላለሻ ቦቴ መኪና ተከራይቶ በድምሩ ብር 540,000.00 ለተጨማሪ ወጪ የተዳረገ ከመሆኑም በላይ ወጪው አሁንም የቀጠለ መሆኑ፤
2. ኮሌጁ ከሁሴን ኢብራሂም ህንጻ ሥራ ተቋራጭ ጋር በብር 9,221,913.25 የመኖሪያ ቤት ግንባታ ውል የፈጸመና ሥራው ተጠናቆ ርክክብ የተከናወነ ቢሆንም ለግንባታው የመጸዳጃ ቤት ፍሳሽ ማስወገጃ አብሮ

ስላልተገነባለት ያለአገልግሎት ከሁለት ዓመታት በላይ ተቆልፎ የሚገኝ መሆኑ፤

3. ኮሌጁ ኤፍ ኤ ዋይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር ጋር በብር 5,468,710.00 የህንጻ ጥገና ግንባታ ውል የፈጸመ ሲሆን፣ ጥገናው ከመጋቢት 2006 ዓ.ም ጀምሮ በስምንት ወራት ውስጥ ማለቅ እንዳለበት ቢጠቀስም ግንባታው ከመዘግየቱም በተጨማሪ የጥገናው ሥራ የተቋረጠ ቢሆንም ምንም ዓይነት ህጋዊ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

## 3.4.2 ሥጋት

- መንግሥትን ለተጨማሪ ወጪ ይዳርጋል፡፡
- የመንግሥት ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ አይቻልም፡፡
- የግንባታው ወጪታማነት ጥያቄ ውስጥ ሊገባ ይችላል፡፡
- የክትትልና የቁጥጥር ክፍተት መኖሩን ሊያመለክት ይችላል፡፡

## 3.4.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ከፍተኛ ገንዘብ ወጥቶባቸው እየተገነቡና እየተጠገኑ ያሉ ግንባታዎች የችግሩ ምንጭ ተጣርቶ መጠገን ያለባቸው ተጠግነው ተጨማሪ ግንባታ ለሚፈልጉትም አስፈላጊው ግንባታ ተደርጎላቸው ወደ አገልግሎት እንዲገቡ እንዲደረግ ወይም ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች እንዲወሰድ መደረግ ይኖርበታል፡፡

## 3.4.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

1. በአሊ ሞሚን በተዘረጋዉ የዉሃ መስመር ላይ የተፈጠረዉን ችግር ለማጣራት ለፕሮጀክቱ አማካሪና ከአፋር የዉሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ጋር ደብዳቤ ተጻጽፈን፡-

   ሀ. የአፋር ዉሃ ስራዎች ቱቦዎቹን ያፈረሰዉ አስፈቅዶና መልሶም ሊጠግን እንደማይችል እና ሆኖም በገዋኔ የሚገኘዉን የዉሃ ቱቦ ለኮሌጁ የሚያስረክብ መሆኑን፤

ለ. አማካሪዉ የዉሀ ቢሮም በርክክቡ ወቅት በሪማርክ የተመዘገቡ ግድፈቶችን ጨምሮ በስራ ተቋራጩ አስፈላጊዉ ማስተካከያ እንደሚደረግ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ይሁንና የተፈጠረዉን ችግር ለመፍታት ባለቤት የሆነዉ ሥራ ተቋራጭ የዉል ግዴታዉን እንዲወጣ የማድረግ ኃላፊነት እንዳለበት በማሳሰብ እንዲያዉቁትና አፈፃፀሙንም በህጋዊ አግባብ በመውሰድ እርምጃ በመውሰድ የምናሳውቅ ይሆናል፡፡

2. ኤፍ ኤ ዋይ ኮንስትራክሽን የጥገና ስራዉ ተጀምሮ ለረጅም ጊዜ የተጓተተዉ የጥገና ሥራዉ በከፍተኛ ፍጥነት እየተካሄደ እያለ ለስራ ተቋራጩ የሚቀሩ ክፍያዎች በ2007/2008 በጀት ዓመት ሳይለቀቅ በመቅረቱና እንዲሁም ስራዉን ለመከታተል የተመደበዉ መሀንዲስ በስራ ተቋራጩ የዉለታዉ የስራ ዝርዝር የሌሉና በተጨማሪ የሚከናወኑ ተግባራትን በልዩነት ታይቶ እንዲወሰንለት የሚጠበቅበትን ኃላፊነት ባለመወጣቱ በቢሮዉ በኩል በተለይም መሀንዲስ እስኪመደብ ድረስ ሰፊ ግዜ የወሰደ በመሆኑ ሲሆን፣ በመጨረሻ ለአማካሪ ቢሮዉ በሰጠነዉ ማሳሰቢያ መሠረት ሌላ መሀንዲስ ተመድቦለት የግንባታዉ የመጨረሻ ደረጃ ድረስ እያለ ከህንፃዉ ጋር ተያያዥ የሆኑ የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ጥገና እንደሚያስፈልገዉ በመግለጽ ለሂደቱ አስፈላጊዉ የዲዛይን ጥናት ስራ ተወስኖ ቅድሚያ ክፍያዉ በመዘግየቱ የሚጠቀሱ ምክንያቶች ናቸዉ፡፡ ይሁንና በ2010 ዓ.ም ቀሪ ስራዎች እስኪጠናቀቁ ድረስ ግዜያዊ ርክክብ እንዲደረግልን ለአማካሪዉ ጥያቄ አቅርበን ቢሮዎቹን እየተገለገልን ሲሆን ለስራ ተቋራጩ የቀረበዉ የክፍያ በጀቱ እንደተለቀቀ የተቋረጠዉ ስራ ተጀምሮ እንዲጠናቀቅ ተገቢዉን እርምጃ ለመዉሰድ በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን፡፡

## 3.5 ኮሌጁ የግዢ እቅድ ያላዘጋጀ መሆኑ፤

### 3.5.1 ግኝት

ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣዉ የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 3 አንቀፅ 8 ቁጥር 1 ማንኛውም የመንግሥት መ/ቤትና በስሩ የተደራጁ አካላት የታቀዱ የስራ

ፕሮግራሞቻቸዉን ተግባራዊ ለማስደረግ የሚያስፈልጋቸዉን ግዥ በወቅቱ ለመፈጸም የሚያስችል በመርሃ ግብር የተደገፈ የግዥ ዕቅድ ማዘጋጀት እንደሚገባና ዕቅዱም ለግገር ኤጀንሲ መላክ እንዳለበት ይደነግጋል። ሆኖም ኮሌጁ በ2009 በጀት ዓመት የግዥ እቅድ ያላዘጋጀ እና ለግገር ኤጀንሲ ያላከ መሆኑ ታውቋል።

### 3.5.2 ***ሥጋት***

ያለእቅድ የሚገዛ ግዥ የመንግሥት ገንዘብ ያላግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

### 3.5.3 ***የማሻሻያ ሃሳብ***

በግዥ አፈጻጸም መመሪያው መሰረት የግዥ እቅድ በማዘጋጀት በኮሌጁ ኃላፊ ፀድቆ ለግዥ ኤጀንሲ መላክ ይኖርበታል።

### 3.5.4 ***የሥራ አመራሩ ምላሽ***

በክፍሉ ሥር በሚገኙ የሰዉ ኃይል እጥረት እና ለየሥራ ክፍሉ መቅረብ የሚገባቸዉ የዕቃ ግዥ ፍላጎት መዘግየት ዕቅዱን በወቅቱ ለማቀድ አላስቻለም።

### 3.5.5 ***የኦዲተሩ አስተያየት***

ኮሌጁ የክፍሉን የሰው ኃይል በማሟላት የግዥ ዕቅዱን በወቅቱ እያዘጋጀ ለሚመለከታቸው አካለት ሁሉ መላክ ይኖርበታል።

# 4. ***ንብረት***

## 4.1 ***በንብረት አያያዝ ላይ የታዩ ክፍተቶች***፤

### 4.1.1. ***ግኝት***

1. የኮሌጁ የንብረት አስተዳደር በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1.1. የጄኒሬተር ማስቀመጫ ቤቶች ግድግዳቸው እና ጣሪያቸው እየተሰነጠቀ የሚገኝ መሆኑ፤

1.2. የኮሌጁ ላይብረሪ ጣሪያ የሚያፈስ መሆኑ፤

1.3 መምህራንና ሰራተኞች መኖሪያ ህንጻዎች ላይ የተገጠመው መቀዝቀዣ (ኤሲ) ሁሉም በአብዛኛው የማይሰራ መሆኑ፤

1.4. በሁሉም ግምጃ ቤቶች ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡና የማይሰጡ ንብረቶች ተቀላቅለው የተቀመጡ ከመሆናቸውም በላይ በዓይነት ያልተለዩና ለቆጠራ በማያመች መልኩ አንዱ በአንዱ ላይ ተደራርበው የሚገኙ መሆኑ፤

1.5. ሊወገዱ የሚገባቸው 13 ጠርሙስ ሰልፈሪክ እና 10 ጠርሙስ ሃይድክሎሪክ አሲድ የሚገኝ መሆኑ፤

1.6. በነዳጅና ቅባት ግምጃ ቤት ውስጥ የእሳት ማጥፊያ የሌለ መሆኑ፤

1.7. በኮሌጁ እስቶክ ካርድና ቢን ካርድ የተዘጋጀ ቢሆንም በተሟላ መልኩ ምዝገባው ያልተካሄደ መሆኑ፤ (ለምሳሌ የተማሪዎች ካፍቴሪያ የምግብ ጥሬ እቃ ግምጃ ቤት ሙሉ በሙሉ፣ የተማሪዎች ክልኒክ የፋርማሲ ዕቃዎችና ደስታ ወረቀት ይጠቀሳሉ)

1.8. አገልግሎት የማይሰጡ በርካታ ንብረቶች ( ወደ ዘጠና የሚጠጉ የማያገለግሉ የመኪና ጎማዎች እንዲሁም 25 ፎቶ ኮፒ ማሽን፣ 30 የሚሆኑ ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮች 34 የሚሆኑ ዴስክቶፕ ኮምፒዩተሮች ከነፕሮሰሰሩና ከኬብሎቹ ጋር) እንዲወገዱ ያልተደረገ መሆኑ፤

1.9. በውድ ዋጋ የተገዙ ሁለት ጄኒሬተሮች ከህንጻው ግንባታ ጋር በሰንሻይን ድርጅት የተተከሉ ቢሆንም ከመጡበት ቀን ጀምሮ ያለአገልግሎት የቆሙ መሆኑ፤

1.10. ወደ ስድስት የሚሆኑ ጄኒሬተሮች በብልሽት ምክንያት ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

1.11. የቋሚና አላቂ እቃዎች ምዝገባ ወቅታዊ ያልተደረገ መሆኑ፤

1.12. የቋሚ ንብረት መመዝገቢያ ካርድና መዝገብ በተሟላ መልኩ ያልተያዘ መሆኑ፤

1.13. በርዳታና በስጦታ የመጡ እቃዎች ዋጋ ያልተተመነላቸው መሆኑ፣

1.14. ሰኔ 10 ቀን 2004 ዓ.ም በቋሚ ንብረት መጠየቂያና ወጪ ማድረጊያ ደረሰኝ ቁጥር 000245 በአቶ ዳኛቸው መኩሪያ የወጣው ቶሺባ ላፕቶፕ ኮምፒዩተር የጠፋ ሲሆን፣ ኮሌጁ ንብረቱን እንዲከፍሉ ለግለሰቡ ደብዳቤ የጻፈላቸው ቢሆንም ግለሰቡ የንብረቱን ዋጋ መክፈል አለመጀመራቸው፤

1.15. አቶ ጌታሁን ግርማ ህዳር 28 ቀን 2005 ዓ.ም በንብረት ወጪ ደረሰኝ ቁጥር 000268 ዲጂታል ካሜራ እንዲሁም መጋቢት 23 ቀን 2003 ዓ.ም በንብረት ወጪ ደረሰኝ ቁጥር 000134 ላፕቶፕ ኮምፒተር በስማቸው ያወጡ ሲሆን፣ ከሥራቸው በ2006 በጀት ዓመት ሲለቁ ያወጡትን ካሜራ ተመላሽ ለማድረጋቸው ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1.7 እስከ ተራ ቁጥር 1.15 በተመለከቱት ግኝቶች ላይ ተገቢው ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በ2007 በጀት ዓመት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

### 4.1.2. <u>ሥጋት</u>

- ☞ ኮሌጁ መንግሥት ባወጣዉ የንብረት አስተዳደር አዋጅና መመሪያ መሰረት የማይፈጸም ከሆነ ለውስጥ ቁጥጥር ስርዓት መዳከም ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡
- ☞ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ ያለመውሰድ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

#### 4.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

- ✓ አገልግሎት የሚሰጡትና የማይሰጡት ንብረቶች ተለይተው በአግባቡ ሊቀመጡ ይገባል፡፡ ሊወገዱ የሚገባቸው ንብረቶችም በመመሪያው መሰረት ሊወገዱ ይገባል፡፡
- ✓ መሥሪያ ቤቱ በኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት አስፈላጊው እርምጃ መውሰድ እንዳለበት በድጋሚ እናሳስባለን፡፡

#### 4.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

1. በኮሌጁ ለረዥም ጊዜ አገልግሎት ሲሰጡ ቆይተው በብልሽት የቆሙና በጥገናም ተስተካክለው አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ ተሽከርካሪዎችና ትራክተሮች መኖራቸውን በመጥቀስ እንዲወገዱልን ለመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ያሳወቅን ቢሆንም በወቅቱ ያላስተላለፍነው መረጃ የተጠቀሱትን ትራክተሮችና ተሽከርካሪዎች ለማስወገድ የአሰራር ስርዓቱ የሚጠይቀው ዝርዝር መረጃና ታሪክ የተሟላ ባለመሆኑ ተፈላጊ መረጃውን አሟልተን እንድንልክ በመጠየቃችን የማስወገድ ሥራው ሊዘገይ ችሏል፡፡ ይሁንና የተጠቀሱት መሣሪያዎችና ትራክተሮች ከሃያ እና ሰላሳ ዓመታት በላይ በሚቆጠር ዕድሜ በኮሌጁ ስለመገኘታቸው እንጂ የንብረቱ ባለቤትና ከየት እንደመጡ የሚያስረዳ የሰውም ሆነ የሠነድ ማስረጃ ፈልገን ለማግኘት እንደማንቍል በመግለጽ ንብረቱ እንደስክራፕ ብረታ ብረት ተቆጥረው እንዲወገዱ ያለንን አስተያየት አሳውቀን በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን፡፡
2. በየቦታ ተበታትነው የሚገኙ ልዩ ልዩ ብረታ ብረቶች የተሽከርካሪ ጎማና ባትሪ፣ መድሃኒቶች፣ ቶነሮች የህትመትና የጽህፈት መሣሪያዎችና አክሰሰሪዎች በአይነታቸው የመለየት እና የአወጋገድ ሥርዓቱ የሚጠይቀውን መረጃ በማሟላት ላይ እንገኛለን፡፡

3. በኮሌጁ የዕቃ ግምጃ ቤት የታየውን የአደረጃጀት ችግር በተመለከተ ለተሰጠው አስተያየት በመጋዘን የሚገኙ ዕቃዎች ከአገልግሎታቸው እና ባህሪ አንጻር የአቀማመጥ ስርዓቱን ጠብቀው መልክ እንዲይዙ የተጀመረው ሥራ ተጠናቋል።

#### 4.1.5. የኦዲተሩ አስተያየት

በንብረት አስተዳደሩ ላይ የታዩ ክፍተቶችን ለማስተካከል የተደረገው እና እየተደረገ ያለው ጥረት ተጠናክሮ እንዲቀጥል እያሳሰብን እርምጃ ተወስዶባቸዋል የተባሉ ክፍተቶች ላይ እርምጃ ለመወሰዱ በቀጣይ ኦዲት ወቅት የሚረጋገጥ ይሆናል።

## 5. በጀት

### 5.1 ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት ያልተሰራበትና ከበጀት በላይ የወጣ ሂሳብ፤

#### 5.1.1 ግኝት

ለኮሌጁ በ2009 በጀት ዓመት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው የካፒታል ወጪ በጀት አጠቃቀም በየሂሳብ ኮዶቹ ሲታይ ከ10% በላይ ብር **6,371,045.11** ሥራ ላይ ያልዋለ ሲሆን፣ ብር **108,363.79** ደግሞ ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ መሆኑ ታውቋል።

(ዝርዝሩ አባሪ 8 ተያይዟል)

#### 5.1.2 ሥጋት

☞ የበጀት ዝውውር ሳይፈጸም ለየሒሳብ መደቦቹ ከተደለደለው በጀት በላይ ክፍያ መፈጸም ተጠያቂነትን ሊስከትል ይችላል።

☞ የወጪ ሂሣብ በጀቱ በዕቅዱ መሠረት አለመፈፀሙ የኮሌጁን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል።

### 5.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ኮሌጁ የበጀት ዕጥረት ካጋጠመው በቅድሚያ የበጀት ሕጉን ተከትሎ የበጀት ዝውውር መጠየቅ ይኖርበታል። ከዚህም በተጨማሪ ሐገሪቷ ያላትን ውስን በጀት በማብቃቃት በተገቢው ሥራ ላይ ማዋል ይቻል ዘንድ በተለይም በጎላ ሁኔታ ጥቅም ላይ ሳይውሉ በቀሩት የሂሳብ ኮዶች ላይ በበጀት እቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

### 5.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

ለኮሌጁ የቀረበዉ የክፍያ መጠይቅ በወቅቱ የነበሩት የኮሌጁ ኃላፊ እንዲነሱ ሲደረግ እሳቸዉን የሚተኩ ኃላፊ እስኪሰየም ድረስ በነበረዉ የሽግግር ጊዜ መዘግየት ሳቢያ ዝዉዉር የተጠየቀላቸዉና በሰነድ የቀረቡ የወጪ ማስረጃዎች በጀቱ ተፈቅዶ ሳይለቀቅ በመቅረቱ በጀቱ ሊተርፍ የቻለ ሲሆን፤ ለአመቱ ከተለቀቀ በጀት በላይ ክፍያ የተፈፀመው የዶሮ እርባታ ግንባታ ኮሌጁ ከስራ ተቋራጩ ጋር በገባዉ ዉል እና በስራዉ ሂደት ግንባታዉ የሚገኝበትን ደረጃ ገምግማ እንዲከፈል በአማካሪዉ የቀረበዉን የክፍያ መጠይቅ መነሻ በማድረግ በጀቱ እንዲለቀቅ ለማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቱ ያቀረብነዉ ጥያቄ ተፈፃሚ ይሆናል በሚል እምነት ለስራ ተቋራጩ እንዲያውቀዉ ከተደረገ በኋላ የበጀት ዓመቱ ተጠናቆ በግረስ ፔሬድ ይለቀቃል ብለን በመጠባበቅ ላይ እያለን በጀቱ ሳይለቀቅ በመቅረቱ በስራ ተቋራጩ የተጀመሩ ስራዎች ከፍጻሜ ለማድረስ ሲባል ስህተት ቢሆንም ከተመላሽ በጀት ሊንከፍል የቻልን መሆኑን እየገለጽን ይህን መሰል ችግር በቀጣይ ላለመድገም ተምረንበታል።

### 5.1.5 የኦዲተሩ አስተያየት

ኮሌጁ የበጀት እጥረት ካጋጠመው በቅድሚያ የበጀት ህጉን ተከትሎ ዝውውር መጠየቅ ይገባዋል። ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ ክፍያ መፈጸም ተቀባይነት የሌለው ከመሆኑም በተጨማሪ ተጠያቂነትን ሊያሥከትል እንደሚችል መታወቅ ይኖርበታል።

ከዚህም በተጨማሪም መሥሪያ ቤቱ የበጀት አጠቃቀሙ ላይ ክትትል በማድረግ እና የማይጠቀምበትን በጀት ለይቶ በማውጣት የበጀት እጥረት ላለባቸው መሥሪያ ቤቶች የበጀት ዝውውር ተደርጎ ጥቅም ላይ እንዲውል ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ማሳወቅ እንዲቻል ሁኔታውን ለማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቱ ማሳወቅ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን።

## 6. <u>ልዩ ልዩ</u>

### 6.1 <u>በ2007 በጀት ዓመት ግኝቶች ላይ በተሰጡት የኦዲት አስተያየቶች መሰረት እርምጃ ያልተወሰደ ስለመሆኑ</u>፤

#### 6.1.1 <u>ግኝት</u>

የፌዴራል ዋና ኦዲተር የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ መግለጫዎችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን በተሰጠው አስተያየት መሰረት ተገቢው እርምጃ የተወሰደ መሆኑ ሲጣራ፡-

1. በኮሌጁ የተሽከርካሪ ሥምሪት፣ አያያዝና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሰረት፡

   - ✓ በተሽከርካሪዎቹ ሁለቱም የፊት በሮች ጎን ላይ የኮሌጁን ስም የሚያመለክት መለያ ወይም አርማ ያልተለጠፈ መሆኑ፤
   - ✓ አንድ ባልትራ ትራክተር በኮሌጁ ግቢ ውስጥ ብልሽት ምክንያት ከአንድ አመት በላይ ያአገልግሎት ጸሀይና ዝናብ እየተፈራረቀበት ቆሞ የሚገኙ መሆኑ፤
   - ✓ ላንድሮቨር ታርጋ ቁጥር 21350 አ.አ እንዲሁም አራት ሞተር ሳይክሎች ታርጋ ቁጥራቸው 0197, 0198, 0199, 5232 ሊብሬ የሌላቸው መሆኑ፤
   - ✓ ላንድሮቨር፣ ሚትስቡሽ፣ ጃጓር የታርጋ ቁጥር 21350 አ.አ፣ 24593 አ.አ እና 27524 አ.አ እንዲሁም የተወሰነ ክፍላቸው የቀረ ሁለት

ትራክተሮች ከ5 አመት በላይ ሳይወገዱ በሰርቶ ማሳያ ግቢ ውስጥ ጸሀይና ዝናብ እየተፈራረቀባቸው የሚገኙ መሆኑ፤

- ✓ በኮሌጁ ስም የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ያልተዘጋጀላቸው 6 መኪኖች የሚገኙ መሆኑ፤

(ለዝርዝሩ አባሪ 9 ተያይዟል)

2. ጥቅምት 10 ቀን 2007 ዓ.ም በተዘጋጀው የሳጥን ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0827649 ወ/ት ዘውዴ ግርማ ነሀሴ 23 ቀን 2006 ዓ.ም በጻፉት ደብዳቤ መሰረት በሰራተኛና አስተዳደር ሪከርድና ማህደር ዋና ክፍል ውስጥ የተለያዩ ደብዳቤና እንዲሁም የደረጃ እድገት፣ ቅጥርና፣ በተደራቢነት የተለያዩ ክፍሎችንና የንብረት ቆጠራ እንዲሁም በምሽት ጭምር እንደሚሰሩ ጠቅሰው ለዚህም የማበረታቻ ክፍያ እንዲከፈላቸው በጠየቁት መሰረት ተጠቃሽዋ ናዝሬት ለስራ ጉዳይ እንደሄዱ በማስመሰል የአስር ቀን ዉሎ አበል ብር 1250.00 እንዲሁም የትራንስፖርት አበል ብር 300.00 በድምሩ ብር 1,550.00 እንዲከፈላቸው የተደረገ መሆኑ፤

3. በናሙና ከተመረጡት ሰራተኞች ውስጥ 85 የጥበቃ ሠራተኞችና 1 ገንዘብ ያዥ ዋስትና (ተያዥ) እንዲያቀርቡ ያልተደረገ መሆኑ፤

ተገልጸ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ አሰተያየት የተሰጠ ቢሆንም የተወሰደ እርምጃ ያለመኖሩ ታውቋል፡፡

### 6.1.2 *ሥጋት*

ኮሌጁ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት በወቅቱ የማስተካከያ እርምጃ የማይወሰድ ከሆነ፡-

- ☞ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡
- ☞ ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም፣ ለመንግሥት ገንዘብና ንብረት መባከን እና አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

### 6.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ

በኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት አስፈላጊው እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል። ለወደፊቱም በኦዲት ሪፖርት በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት ተገቢው እርምጃ ለመወሰዱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት በድጋሚ እናሳስባለን።

### 6.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

- ✓ ቀደም ሲል በተሰጠን አስተያየት መሠረት የኮለጁ ተሽከርካሪዎች የኮለጁ አርማ አሳትመን የነበረ ቢሆንም በህትመት ጥራት ጉድለት ምክንያት ከተለጠፈበት ሊለቅ ችሏል። ሆኖም ግን አሁን ጥራቱን የጠበቀ ሰቲከር ለማሰራት በህትመት ላይ ይገኛል።
- ✓ ካለን የበጀት ውስንነት አንፃር ቪታራ ትራክተር (Vitra Tractor) ተበላሽቶ ከቆመበት አስጠግኖ ሥራ ላይ ማዋል ሳንችል ቆይተናል። ነገር ግን በ2010 በጀት ዓመት በጀት አስይዘን ለማስጠገን እና ወደ ሥራ ለማሰማራት በእቅድ ላይ እንገኛለን።
- ✓ ዲክላራሲዮን የሞተሮችን ፈልገን ስላጣን ከመንገድ ትራንስፖርት ጋር በመጻጻፍ ችግሩን ለማስተካከል እየተሞከረ ነው።
- ✓ የሚወገዱ የተለያዩ የኮሌጁ ተሽከርካሪዎችን ለረጅም ጊዜ ለጸሀይና ዝናብ ብሎም ለጎርፍ ተጋልጠው ከሆኑበት ቦታ ለማስወገድ አመቺ ወደ ሆነ ደረቃማ ቦታ አሰባስበናል። የማስወገድ ስራውን ለማከናወን ከግዢና ንብረት ማስወገድ ኤጀንሲ ጋር በመጻጻፍ ውሳኔውን በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን።
- ✓ ተሽከርካሪዎቹ በኮሌጁ ስም የመለያ መታወቂያ ለመስጠት ለሚመለከታቸው አካላት ደብዳቤ ጽፈን ውሳኔዎችን በመጠባበቅ በዝግጅት ላይ እንገኛለን።
- ✓ የማበረታቻ ክፍያን በተመለከተ ጉዳዩ የሚመለከተዉ ሰራተኛ ከኮሌጁ የለቀቁ መሆኑን ቀደም ሲል የገለጽን ቢሆንም አሁንም የመንግሥት

ገንዘብ ተመላሽ እንዲሆን አድራሻዉን እያፈላለግን በጥረት ላይ እንገኛለን።

- ✓ በኮሌጃችን በዋና እና ረዳት ገንዘብ ያዥ መደቦች ላይ የቅጥር ማስታወቂያ ያወጣንና በተለይ በረዳት ገንዘብ ያዥ መደብ ላይ የተወዳደረችዉን በዚህ ወር ስራ ለማስጀመር በሂደት ላይ በመሆናችን በጊዜያዊነት ከሶስት ወር ላልበለጠ ጊዜ የምናሰራትን (በዝዉዉር በገንዘብ ያዥነት) የመዝገብ ቤት ሰራተኛ ዋስትና እንድታቀርብ ማድረጉ የስራ ተነሳሽነቷን እንዳይቀንስ በመፍራት እንደሆነና በሌላ በኩል በአርብቶ አደር አከባቢ (በተለይ በኛ ክልል) ሰራተኞችን በተለይ የጥበቃ ሰራተኞችን ዋስትና (ተያዥ) ማስሞላት አስቸጋሪ መሆኑ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም ዘንድ ይታወቃል። ይሁንና ህጉን ተፈፃሚ ከማድረግ አንፃር የአካባቢዉ በዓልን መሠረት ባደረገ መልኩ የጎሳ ተጠሪዎችን ያካተተ ተያዥ እንዲያቀርቡ ለማድረግ ከጎሳ መሪዎች ጋር ስምምነት ላይ በመድረሳቸዉ በቅርቡ ተያዥ ያላቀረቡ በሂደት ተፈፃሚ ይሆናል ብለን እናምናለን።

### 6.1.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

- ✓ ተሸከርካሪዎች ተጠግነው ሥራ ላይ እንዲውሉ አገለረግሎት መስጠት የማይችሉት ደግሞ እንዲውገዱ፣
- ✓ አለአግባብ የተከፈለው የመንግሥት ገንዘብ ለማስመለስም ሆነ ተያዥ ያላቀረቡ ሠራተኞችን ተያዥ እንዲያቀርቡ፣

የተጀመረው ጥረት ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

## 6.2 <u>የጥሬ ገንዘብና የአላቂ እቃ የፈሰስ ሪፖርት ያልተዘጋጀ ስለመሆኑ</u>፤

### 6.2.1 <u>ግኝት</u>

በፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 3/2003 አንቀጽ 35 ተራ ቁጥር 3 መሰረት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ የሚደረግ ሂሳብ ለ/ ላይ ከመንግስት ግምጃ ቤት የገንዘብ ምንጭ ለመደበኛ ሥራ ማስኬጃ በቅድሚያ በሰነድ ተከፍሎ ሳይወራረድ በየዓመቱ

መጨረሻ በሣጥን ከተቆጠረው ውስጥ ክፍያው በበጀት ዓመቱ የተፈጸመና አገልግሎቱ በተከታዩ በጀት አመት ውስጥ የሚሰጥ አላቂ ንብረት ሂሳብ በፈሰስ ሂሳብ ሊመዘገብና ለገ/ኢ/ት/ሚ ፈሰስ ሊደረግ እንደሚገባ ያመለክታል። ይሁን እንጂ የኮሌጁ የውስጥ ኦዲት ክፍል በ2009 በጀት አመት መጨረሻ የጥሬ ገንዘብና የአላቂ እቃ የፈሰስ ሪፖርት ያላዘጋጀና ሂሳቡም በመመሪያው መሰረት ለሚመለከተው አካል ገቢ ያለመደረጉ ታውቋል።

### 6.2.2 ሥጋት

- ☞ የመንግሥት ገንዘብ የበጀት ህጉን ተከትሎ ጥቅም ላይ እንዳይውል ሊያደርግ ይችላል።
- ☞ ከቀጣዩ በጅት ዓመት ላይ ሊቀነስ የሚገባውን በጀት እንዳይቀነስ ሊያደርግ ይችላል።
- ☞ መመሪያውን ተከትሎ ያለመፈጸም ተጠያቂነትን ሊያሥከትል ይችላል።

### 6.2.3 የማሻሻያ ሃሳብ

በመመሪያው መሰረት የበጀት ዓመቱ የጥሬ ገንዘብና የአላቂ እቃ የፈሰስ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት መደረግ ይኖርበታል።

### 6.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

- ♦ በ2009 የበጀት ዓመት ማጠናቀቂያ ላይ በተመላሽ ፈሰስ መሆን የነበረበት ጥሬ ገንዘብ በሚመለከት በወቅቱ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መግባት የነበረበት ተከፋይ ሂሳብ በመሆኑ ነዉ።
- ♦ በሌላ በኩል የአላቂ ዕቃዎች የፈሰስ ሪፖርትን በተመለከተ እስከአሁን በኮሌጁ የነበረው ልምድ በአጠቃላይ የአላቂና የቋሚ ዕቃዎች አመታዊ የንብረት ቆጠራን ሪፖርት ማድረግ እንጂ አላቂ ዕቃዎችን ብቻ በመለየት በሪፖርት አሳዉቀን አናዉቅም። ይሁንና በዓመቱ መጨረሻ የተመዘገቡ አላቂ ዕቃዎች በዕለት ተዕለት የስራ እንቅስቃሴ የሚፈልጉ ሳይሆኑ አልፎ አልፎ የምንጠቀምባቸዉ ናቸዉ።

### 6.2.5 የኦዲተሩ አስተያየት

ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ፈሰስ መደረግ ያለበት የተከፋይ ሂሳብ በሳጥን በጥሬ ገንዘብ ተቀምጦ ከሆነ በወቅቱ ክፍያው መፈጸም ነበረበት፡፡ በሌላ በኩል ኮሌጁ አላቂ እቃዎችን በዕለት ተዕለት የሥራ እንቅስቃሴውም ሆነ አልፎ አልፎ ቢጠቀምባቸውም በመመሪያው መሰረት በአመቱ መጨረሻ ላይ ያሉትን አላቂ እቃዎች በመቁጠር የፈሰስ ሪፖርት ለሚመለከተው አካል ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 6.3 ኮሌጁ ስትራቴጂክ ዕቅድ ያላዘጋጀ ስለመሆኑ፤

### 6.3.1 ግኝት

አንድ ተቋም ምንም ዓይነት የተግባር ስራ ከመጀመሩ በፊት ሊሰራቸው የሚገቡትን ስራዎችና ሊደርስበት የሚያስበውን ደረጃ ማቀድና የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድ በማውጣት ስራ መጀመር እንዳለበት ይታወቃል፡፡ ሆኖም ኮሌጁ የተሰጠውን ተልኮ በአግባቡ ለመምራት የሚያስችል የስትራቴጂክ እቅድ ያላዘጋጀ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

### 6.3.2 ሥጋት

- ኮሌጁ በእስትራቴጂክ እቅድ የማይመራና አመታዊ እቅድ ከአስትራቴጂክ እቅድ አንጻር የማይዘጋጅ ከሆነ የተቋቋመበትን አላማ ለማስፈጸም ሊቸገር ይችላል፡፡
- የተሰራውን ሥራ ለመለካት አያስችልም፡፡

### 6.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ

ኮሌጁ ከተቋቋመበት አላማ አንጻር ስትራቴጂክ እቅድ በማዘጋጀት ለአመታዊ እቅድ መሰርት እንዲሆንና ሰራተኞቹም እቅዱን ተረድተውት ስራቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

### 6.3.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

በኮሌጁ የዕለት ተዕለት የሥራ እንቅስቃሴ የሚከናወኑ ተግባራትን የሚታዩ የአሰራርና አቅርቦት ማነቆዎችን በአጭር፣ በመካከለኛ እና በረጅም ጊዜ

ዕቅድ የሚመጡ ግቦችን ማስቀመጥ እንዳለበት ይታመናል። ይሁንና ሥልታዊ እቅዱን በማዘጋጀት ረገድ የሚያስፈልገዉን እዉቀትና ክህሎት እንዲሁም የዉስጥና የዉጭ ሁኔታዎች የሚዳስስ መረጃ የማሰባሰብ፣ የመተንተንና ለመተግበር ከሚጠይቀዉ ጊዜ፣ ወጪና ለሥራዉ የሚመደበዉ የሰዉ ኃይልና አማካሪ የእቅዱ መዘጋጀት ከሚያስገኘዉ ጠቀሜታ አንፃር ተገቢዉን ትኩረት ሳያገኝ በመቅረቱና እንዲሁም ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በፕሮግራም በጀቲንግ ለመካከለኛ ጊዜ የተፃፈዉን እቅድ እንደ እስትራቴጂክ እቅድ አድርጎ በመወሰድ ምክንያት ነዉ። ይሁንና የኮሌጁን አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋና ዉጤታማ በማድረግ ረገድ የእስትራቴጂክ እቅድ ዝግጅት አስፈላጊነት በመረዳት በያዝነዉ ዓመት የኮሌጁን የመካከለኛ ዘመን እስትራቴጂክ እቅድ አዘጋጅተን ወደ ስራ ለመግባት ተወስኗል።

## 6.4 በቅጥርና በዕድገት ያልተሞሉ ክፍት የሥራ መደቦች፤

### 6.4.1 ግኝት

ኮሌጁ በዕቅድ የያዛቸውን ተግባራት በአግባቡ ለመፈጸም ይችል ዘንድ ክፍት የስራ መደቦችን በሰው ኃይል መሙላት እንዳለበት ይታመናል፡፡ ነገር ግን ኮሌጁ ከተፈቀደለት 430 የስራ መደቦች ውስጥ በሰው ኃይል የተሞላው 249 ሲሆን 181(42%) የሥራ መደቦች ክፍት መሆናቸው ታውቋል።

### 6.4.2 ሥጋት

የተሟላ የሰው ኃይል ባለመኖሩ ምክንያት ኮሌጁ ዕቅዱን እንዳያሳካ ምክንያት ሊሆን እንዲሁም ተገቢው የስራ ክፍፍል እንዳይኖር በማድረግ በአሰራር ላይ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል።

### 6.4.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ኮሌጁ በመመሪያው መሠረት ክፍት የስራ መደቦችን በቅጥርና በእድገት እንዲሞሉ ማድረግ ይኖርበታል።

### 6.4.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

በኦዲት ግኝቱ ሥጋት ተብሎ በቀረበው ሃሳብ ላይ የሰው ሃብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ትክክለኛነቱን ያምናል፣ ይቀበለዋልም ። ይህንንም አሳሳቢ ጉዳይ ዳይሬክቶሬቱ ቀደም ሲል በመረዳቱ ጥረቶች ሲያደርግ እንደነበር ይታወቃል። ለአብነት ያህልም፡-

1. በ2008 በጀት ዓመት ወሳኝ በሆኑ 18 የስራ መደቦች ላይ በጋዜጣ ማስታወቂያ አውጥቶ የነበረ ሲሆን በድጋሚ በነዚሁ 18 ወሳኝ የስራ መደቦች ላይ የደመወዝ በስምምነት እና በሌሎች 35 የስራ መደቦች ላይ የመጀመሪያ ማስታወቂያ በጋዜጣ ያወጣን ቢሆንም የተገኘ ሰው አልነበረም።
2. በ2009 በጀት ዓመት የኦዲት መውጫ ስብሰባ ላይ ያለብንን አሳሳቢ የሰው ሀይል ችግር ለመቅረፍ ሌሎች አማራጭ መንገዶችን እንደ አማራጭ ለመጠቀም በቀረበው ሃሳብ መሰረት በዝውውርም ሆነ በክልሉና በክልሉ አጎራባች ክልሎች ሠራተኞችን አፈላልጎ ለመግኘት የተደረገው ጥረት አልተሳካም።
3. በዚህ በያዝነው 2010 በጀት ዓመት የሰራተኞችን ትኩረት ይስብ ይሆናል በሚል ካለው የደመወዝ ስኬል አምስት (5) እርከን ገብተን በ22 ወሳኝ የስራ መደቦች ላይ የቅጥር ማስታወቂያ በጋዜጣ አውጥተን ልናገኝ የቻልነው 2(ሁለት) ሰራተኞችን ብቻ ነው።

ስለዚህ የግኝቱን ትክክለኛነትና የስጋት ምንጭነቱን እያረጋገጥን ችግሩን ለመቅረፍ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ እንዳለብን እናምናለን።

## 6.5 የሥጋት ተጋላጭነት ግምገማ ያልተደረገ ስለመሆኑ፤

### 6.5.1 ግኝት

በፌዴራል መንግሥት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 መሰረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተቋቋሙበትን ዓላማዎች ለማስፈጸም ዕቅዶችና ዝርዝር የዕለት ተዕለት ተግባራት በማከናወን ሂደት የሚከሰቱ ችግሮችንና የተጋላጭነት ደረጃ ለመለየት የውስጥና የውጪ

ኦዲተሮችንና ሌሎች የሚመለከታቸውን ባለሙያዎች በመጠቀም የሥጋት ምንጮች ዳሰሳ ማካሄድ እንዳለባቸው ተመልክቷል። ሆኖም ኮሌጁ የሥጋት ምንጮች ዳሰሳ፣ የተጋላጭነት ደረጃ መለየት እና የሥጋት ተጋላጭነት ፍተሻ ያላደረገ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል።

### 6.5.2 <u>ሥጋት</u>

የሥጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ ጥናት ተደርጎ የመፍትሄ አቅጣጫ ካልተቀመጠ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ኮሌጁ ዓላማውን እንዳያሳካ እንቀፋት ሊሆኑ ይችላሉ።

### 6.5.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ኮሌጁ የሥጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ በየጊዜው ቢያደርግ በውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማነት የተነሳ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለይቶ ቅድመ ጥንቃቄ ለመውሰድ የሚኖረውን ጥቅም ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በመመሪያው መሰረት የስጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ ማድረግ ይጠበቅበታል። ስለሆነም በመመሪያው መሰረት የሥጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ እንዲደረግ እናሳስባለን።

### 6.5.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

የኮሌጁን ዓላማ ለማሳካት የተመደበዉን ሃብትና የሰዉ ኃይል ከአደጋ ተጋላጭነት ስጋት ለመከላከል የሚያስችል የዳሰሳ ጥናት ሲካሄድ እንዳልነበረና ለጉዳዩም አዲስ መሆናችንን ቀደም ሲል የተገለፀ መሆኑን እያስታወስን፣ ሆኖም ይህንኑ ከመከላከል አንፃር፡-

- ዉስን በሆነ የሰዉ ኃይል የሚንቀሳቀሱ የስራ ክፍሎች ያለዉን ክፍተት ለመሸፈን ለስራ መደቡ ቅርበት ያላቸዉን ቋሚ ሰራተኞች በግዜያዊ ዝዉዉር እንዲሰሩ እየተደረገ ይገኛል።
- ቅጥረ ግቢዉን ለጥበቃና እንዲሁም የስርቆትም ሆነ ሌላ ጥቃት የሚከላከል የአጥር ማጠናከርና የጥበቃ ሠራተኞችን የማንቃት ስራ እየተሰራ ይገኛል

♦ በሌላ በኩል ከአደጋ ተጋላጭነት ስጋት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸዉ የስራ መሣሪያዎች፣ ትጥቆችና አልባሳት እንዲሁም ከመርዛማ ኬሚካሎች ጋር ግንኙነት ያላቸዉ ሠራተኞችን ሊገጥማቸዉ የሚችለዉን የጤና ችግር ለመቀነስ እንዲቻል ወተት የሚያገኙበትን ሁኔታ በማጥናት እንዲፈቀድ የተለያዩ ስራዎችን ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ጋር በመስራት ላይ እንገኛለን። የደንብ ልብስና የስራ ትጥቆችም በጥናት ላይ የተመሠረተ አቅርቦት እንዲኖር ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር እንቅስቃሴ ተጀምሯል።

### 6.5.5 የኦዲተሩ አስተያየት

የሥጋት ተጋላጭነት ግምገማ የሚደረገው ኮሌጁ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈፀም በሚያደርገው እንቅስቃሴ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሥጋቶችን በመለየትና ምንጫቸውን በማወቅ፣ የሥጋት ደረጃና (Level of Risk) የተጋላጭነት አቅም (Probability of Occurrence) ተገንዝቦ ይህንን ሥጋት ለመቀነስ ከተቻለም ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋት ነው። ስለሆነም ኮሌጁ በመመሪያው መሰረት ተቋማዊ የሥጋት ተጋላጭነት ግምገማ ቢያደርግ ጠቃሚነቱ የጎላ ይሆናል።

## 6.6 የውስጥ ኦዲት ክፍሉን በተመለከተ፤

### 6.6.1 ግኝት

በፋይናንስ አዋጅ ቁጥር 648/2001 እና በፋይናንስ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 970/2008 በሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 61 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት እና አዋጁንና ደንቡን ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ ቁጥር 47/2009 መሰረት እንዲሁም እያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የዉስጥ ኦዲት ክፍል በየሩብ ዓመቱ የመሥሪያ ቤቱ ሥራ አመራርና ሠራተኞች ኃላፊነታቸዉን በብቃት መወጣት እንዲችሉ በተዘረጋዉ የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በሥራ ላይ ባሉት ህጎችና የአሰራር ሥርዓቶች መሰረት ስራዎች መከናወናቸዉን ኦዲት እያደረገ በመመሪያዉ ላይ በተቀመጡት ግዜ ዉስጥ ለኮሌጁ የበላይ ኃላፊና ለእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ሪፖርት የሚያደርግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ☞ ለውስጥ ኦዲት ክፍሉ በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል 3 ሲሆን አሁን በስራ ላይ የሚገኘው የሰው ኃይል 1 ብቻ መሆኑ፣
- ☞ የውስጥ ኦዲቱ ዓመታዊ የሥራ እቅድ የሌለው መሆኑ፣
- ☞ የውስጥ ኦዲት ሰራተኛው የሂሳብ ሥራ ዝግጅትን ደርቦ የሚሰራ መሆኑ፣
- ☞ የውስጥ ኦዲቱ በገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመሪያ መሰረት የየሩብ ዓመቱ ሂሳብ ኦዲት ያላደረገና ሪፖርት ለኮሌጁ የበላይ ኃላፊና ለእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ያልቀረበ መሆኑ፣

ታውቋል። የውስጥ ኦዲቱን በተመለከተ በ2007 ኦዲት ወቅትም አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም ምንም ዓይነት የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ታውቋል።

### 6.6.2 ሥጋት

- ☞ የውስጥ ኦዲት ክፍሉ በተቀመጠው የግዜ ሰሌዳ መሰረት የኮሌጁን ሂሳብና ንብረት ኦዲት ካላደረገ በቀላሉ ሊቀረፉ የሚችሉ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች ሳይታዩ ሊታለፉ ይችላሉ።
- ☞ የውስጥ ኦዲት ሰራተኛው የሂሳብ ሥራ ዝግጅትን ደርቦ እየሰራ ኦዲት የሚያደርግ ከሆነ የሚሰራው የኦዲት ሥራ ተዓማኒነትና ተቀባይነት ላይኖረው ይችላል።

### 6.6.3 የማሻሻያ ሃሳብ

የውስጥ ኦዲት ክፍሉ በመመሪያው መሰረት አመታዊ እቅድ በማዘጋጀት፣ የተሟላና ብቁ የሆነ የሰው ኃይል በመመደብ (በመቅጠር) በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ኦዲቱን ማከናወን ይኖርበታል። የየሩብ ዓመቱን የኦዲት ሪፖርትን እና ዓመታዊ የፊሰስ ሪፖርትን ለኮሌጁ የበላይ ኃላፊና ለእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ማሳወቅ ይኖርበታል።

### 6.6.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

የክፍሉ የሰዉ ኃይል አለመሟላት ችግር ለተገኘዉ የኦዲት ግኝት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለዉ። በ2007 በጀት ዓመት ኦዲት በተደረገበት ወቅት ክፍሉ

ዉስጥ ያለዉ አንድ የሰዉ ኃይል ነበር። በወቅቱም ነሐሴ 21 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በቢፒአር ድልድል ምክንያት ወደ ሌላ ክፍል እንዲዘዋወር ተደርጓል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ጥቅምት 16 ቀን 2009 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ኮሌጁ የዉስጥ ቁጥጥር ሰራተኛ የሌለዉ በመሆኑ በቋሚ ቅጥር እስኪሸፈን ድረስ በያዙት ስራ ላይ በተደራቢነት የኮሌጁን የዉስጥ ቁጥጥር ስራ እንዲጀምሩ የሚል ደብዳቤ በአድራሻዬ የተጻፈ ሲሆን፣ ነገር ግን የኮሌጁ ፋይናንስና በጀት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የስራ ክፍል ሰራተኛ የሰዉ ኃይል እጥረት እና የስራ ጫና ስላለ በሚል ፋይናንሱን በአጋዥነት እንድረዳ በተደረገዉ መሠረት አብዛኛዉን ጊዜ በስራ የማሳልፈዉ በፋይናንስ ክፍል ዉስጥ ነበር። በአጠቃላይ ለተገኘዉ የኦዲት ግኝት ምክንያቱ በመዋቅሩ መሰረት የተቀመጠ የሰዉ ኃይል አለመኖር ሲሆን ኮለጁ በቀጣይ ክፍሉን በቅጥር አሟልቶ ያለዉን ክፍተት ለመቅረፍ ተገቢዉን ጥረት ያደርጋል።

### 6.6.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

ለውስጥ ኦዲት ክፍሉ የተመደቡት ሰራተኛ የፋይናስ ክፍሉን አብዛኛውን ሥራ በተደራቢነት እያከናወኑና ራሳቸው የሰሩትን ሥራ ኦዲት ሊያደርግ አይችልም። የሙያ ሥነ-ምግባሩም አይፈቅድም። ስለሆነም ለውስጥ ኦዲት ክፍሉ ራሱን የቻለ ባለሙያ እንዲመደብለት መደረግ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን።

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት በኮሌጁ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ስለተደረገልን መልካም የሥራ ትብብር እናመሰግናለን።

**አባሪ. 1**

**<u>የተሰብሳቢ ሒሳብን የቆይታ ጊዜ የሚያሳይ ዝርዝር</u>፤**

| ተራ ቁጥር | የሂሳብ መደብ ቁጥር | የተሰብሳቢ ሂሳቡ ክፍያ የተፈጸመበት ጊዜ | የቆይታው ጊዜ | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ | ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ | |
| 1 | 4203 | ከሰኔ 30 ቀን 2006 ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ | 75,636.52 | 226,541.91 | 302,178.43 |
| 2 | 4211 | ከሰኔ 30 ቀን 2006 ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ | 107,423.21 | 462,408.06 | 569,831.27 |
| **ጠቅላላ ድምር** | | | **183,059.73** | **688,949.97** | **872,009.70** |

**አባሪ .2**

**<u>የተከፋይ ሒሳብን የቆይታ ጊዜ የሚያሳይ ዝርዝር</u>**

| ተራ ቁጥር | የሂሳብ መደብ ቁጥር | ተከፋይ ሂሳቡ የተያዘበት ጊዜ | የቆይታው ጊዜ | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ | ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ | |
| 1 | 5002 | ከየካቲት 28 ቀን 2006 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ | | **1,009.04** | **1,009.04** |
| 2 | 5005 | ከጥቅምት 04 ቀን 2006 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ | **1,293.70** | **4,819.07** | **6,112.77** |
| 3 | 5006 | ከታህሳስ 01 ቀን 2006 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ | **479.65** | **44,305.07** | **44,784.72** |
| 4 | 5028 | ከነሀሴ 12 ቀን 2008 ዓ.ም እሰከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ | **2,175.00** | | **2,175.00** |
| 5 | 5061 | ከሰኔ 12 ቀን 2006 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ | | **120,038.24** | **120,038.24** |
| | | ድምር | **3,948.35** | **170,171.42** | **174,119.77** |

**አባሪ. 3**

<u>በህጉ መሰረት ያልተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሂሳብ ዝርዝር፤</u>

| ታክሱ የተቀነሰበት ቀን | የወጪ ቫወቸር ቁጥር | የገንዘቡ መጠን | ለግብር ሰብሳቢው ባለሥልጣን ገቢ የተደረገበት ቀን |
|---|---|---|---|
| 08/03/2009 | PV 50120 | 1,043.48 | 30/10/2009 |
| 23/03/2009 | PV 50144 | 1,343.48 | 30/10/2009 |
| 26/03/2009 | PV 50150 | 10,468.59 | 30/10/2009 |
| 30/03/2009 | JV 985647 | 880.44 | 30/10/2009 |
| 13/04/2009 | PV 50173 | 12,771.76 | 30/10/2009 |
| 25/04/2009 | JV 985690 | 3,003.74 | 30/10/2009 |
| 25/04/2009 | JV 985691 | 4,115.10 | 30/10/2009 |
| 26/04/2009 | JV 985695 | 18,450.70 | 30/10/2009 |
| 28/04/2009 | JV 985697 | 5,662.27 | 30/10/2009 |
| 29/04/2009 | JV 985699 | 5,572.12 | 30/10/2009 |
| 30/04/2009 | JV 985702 | 3,945.00 | 30/10/2009 |
| 30/05/2009 | JV 985764 | 1,125.00 | 30/10/2009 |
| 06/06/2009 | PV 50235 | 89,142.83 | 30/10/2009 |
| 09/06/2009 | PV 50238 | 12,061.24 | 30/10/2009 |
| 10/06/2009 | PV 50240 | 6,558.17 | 30/10/2009 |
| 10/06/2009 | PV 50244 | 7,445.25 | 30/10/2009 |
| 04/07/2009 | PV 50270 | 331,373.07 | 30/10/2009 |
| 04/07/2009 | PV 50273 | 8,000.68 | 30/10/2009 |
| 15/07/2009 | JV 985817 | 16,650.00 | 30/10/2009 |
| 15/07/2009 | JV 985818 | 15,480.00 | 30/10/2009 |
| 22/07/2009 | PV 50289 | 9,488.57 | 30/10/2009 |
| 22/07/2009 | PV 50290 | 124,048.00 | 30/10/2009 |
| 23/07/2009 | JV 985826 | 1,569.03 | 30/10/2009 |
| 03/08/2009 | PV 50314 | 12,467.68 | 30/10/2009 |
| **ድምር** | | 702,666.20 | |

**አባሪ. 4**

**በህጉ መሰረት ያልተከፈለ የቅድሚያ ግብር ሂሳብ ዝርዝር፤**

| ታክሱ ተቀናሽ የተደረገበት ቀን | የወጪ ቫወቸር ቁጥር | የገንዘብ መጠን | ለአገር ውስጥ ገቢ የተደረገበት ቀን |
|---|---|---|---|
| 03/12/2008 | PV 0829013 | 672.00 | 30/10/2009 |
| 09/12/2008 | PV 51083 | 10,463.40 | 30/10/2009 |
| 25/12/2008 | PV 51097 | 1,710.00 | 30/10/2009 |
| 25/12/2008 | PV 51099 | 2,230.00 | 30/10/2009 |
| 25/12/2008 | PV 51100 | 5,400.00 | 30/10/2009 |
| 10/01/2009 | PV 50066 | 21,300.00 | 30/10/2009 |
| 16/01/2009 | PV 50074 | 19,500.00 | 30/10/2009 |
| 04/02/2009 | PV 50087 | 3,216.00 | 30/10/2009 |
| 14/02/2009 | PV 0829117 | 840.00 | 30/10/2009 |
| 20/02/2009 | PV 50103 | 2,358.00 | 30/10/2009 |
| 23/02/2009 | PV 50106 | 3,533.40 | 30/10/2009 |
| 28/02/2009 | PV 50109 | 3,000.00 | 30/10/2009 |
| 02/03/2009 | PV 50116 | 479.63 | 30/10/2009 |
| 14/03/2009 | PV 50130 | 84.00 | 30/10/2009 |
| 15/03/2009 | PV 50132 | 10,800.00 | 30/10/2009 |
| 15/03/2009 | PV 0829150 | 1,500.00 | 30/10/2009 |
| 26/03/2009 | PV 50148 | 3,600.00 | 30/10/2009 |
| 26/03/2009 | PV 50150 | 5,352.22 | 30/10/2009 |
| 10/04/2009 | PV 0829227 | 1,050.00 | 30/10/2009 |
| 13/04/2009 | PV 50173 | 5,208.46 | 30/10/2009 |
| 20/04/2009 | PV 50181 | 3,000.00 | 30/10/2009 |
| 21/04/2009 | PV 50182 | 3,085.80 | 30/10/2009 |
| 25/04/2009 | JV 985691 | 548.68 | 30/10/2009 |
| 26/04/2009 | JV 985695 | 2,460.10 | 30/10/2009 |
| 28/04/2009 | JV 985697 | 754.97 | 30/10/2009 |
| 29/04/2009 | JV 985699 | 742.95 | 30/10/2009 |
| 30/04/2009 | JV 985702 | 526.00 | 30/10/2009 |
| 15/05/2009 | PV 50212 | 39.00 | 30/10/2009 |
| 15/05/2009 | PV 50216 | 426.09 | 30/10/2009 |
| 16/05/2009 | PV 50215 | 141.00 | 30/10/2009 |
| 25/05/2009 | PV 0829353 | 321.60 | 30/10/2009 |
| 02/06/2009 | PV 50232 | 6,552.00 | 30/10/2009 |
| 02/06/2009 | PV 50234 | 22,794.00 | 30/10/2009 |
| 06/06/2009 | PV 50235 | 5,352.57 | 30/10/2009 |
| 09/06/2009 | PV 50238 | 3,580.21 | 30/10/2009 |
| | **የሚዞር ድምር** | 152,622.08 | |

| ታክሱ ተቀናሽ የተደረገበት ቀን | የወጪቫወችር ቁጥር | የገንዘብ መጠን | ለአገር ውስጥ ገቢ የተደረገበት ቀን |
|---|---|---|---|
| | **የዞረ ድምር** | 152,622.08 | |
| 10/06/2009 | PV  50240 | 874.42 | 30/10/2009 |
| 10/06/2009 | PV 50242 | 11,130.00 | 30/10/2009 |
| 10/06/2009 | PV 50243 | 7,500.00 | 30/10/2009 |
| 10/06/2009 | PV 50241 | 12,870.00 | 30/10/2009 |
| 10/06/2009 | PV 50244 | 992.70 | 30/10/2009 |
| 04/07/2009 | PV 50270 | 20,778.30 | 30/10/2009 |
| 04/07/2009 | PV 50272 | 6,000.00 | 30/10/2009 |
| 04/07/2009 | PV 50273 | 3,061.47 | 30/10/2009 |
| 08/07/2009 | PV 50281 | 3,600.00 | 30/10/2009 |
| 15/07/2009 | JV 985817 | 2,220.00 | 30/10/2009 |
| 15/07/2009 | JV 985818 | 2,064.00 | 30/10/2009 |
| 22/07/2009 | PV 50289 | 4,685.38 | 30/10/2009 |
| 22/07/2009 | PV 50290 | 7,442.88 | 30/10/2009 |
| 22/07/2009 | PV 50293 | 6,480.00 | 30/10/2009 |
| 23/07/2009 | JV 985826 | 209.20 | 30/10/2009 |
| 03/08/2009 | PV 50311 | 300.00 | 30/10/2009 |
| 03/08/2009 | PV 50314 | 5,446.63 | 30/10/2009 |
| 06/09/2009 | JV 985856 | 2,026.09 | 30/10/2009 |
| 09/09/2009 | PV 50407 | 330.44 | 30/10/2009 |
| 09/09/2009 | PV 50408 | 3,987.00 | 30/10/2009 |
| 10/09/2009 | JV 985859 | 545.28 | 30/10/2009 |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **255,165.87** | |

**አባሪ. 5**

**ከሥራ ለለቀቁ ሠራተኞች የተከፈለ ደመወዝ፤**

| ተራ ቁጥር | ቀን | የወጪ ክፍያ ሰነድ ቁጥር | የሠራተኛው ሥም | ሥራ የለቀቁበት ቀን | የደመወዝ ልክ | ያልሰራበት ጊዜ | ተከፍሎ የተገኘ ደመወዝ | መከፈል የሚገባው ደመወዝ | አለአግባብ የተከፈለ ደመወዝ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
